አፍሪካ ቲቪ

16

# አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

## ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት የአጫጭር ሱራዎች አስተምህሮት

(ከሱረቱ ናስ - ሱረቱ ዱሓ)

4

በቴሌግራም

AAcademyEthio

www.AfricaAcademy.com

## سُورَةُ الشَّرۡحِ

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

أَلَمۡ نَشۡرَحۡ لَكَ صَدۡرَكَ ١ وَوَضَعۡنَا عَنكَ وِزۡرَكَ ٢
ٱلَّذِيٓ أَنقَضَ ظَهۡرَكَ ٣ وَرَفَعۡنَا لَكَ ذِكۡرَكَ ٤ فَإِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرًا ٥
إِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرٗا ٦ فَإِذَا فَرَغۡتَ فَٱنصَبۡ ٧ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَٱرۡغَب ٨



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

# ሱረቱ አሽ-ሸርህ

- (የልብ መስፋት ምዕራፍ) የወረደው በመካ ነው፡፡
- የአናቅፅ ብዛት (8) ናቸው፡፡
- **ከምዕራፉ ዓላማዎች፡-**
- አላህ በመልዕክተኛው ላይ መከራን በማንሳት፣ ችግርን በማቅለል፣ ጭንቀትን በማስወገድ እና ሌሎች ውለታዎችን በመዋል ያሚላላቸው መሆኑን የሚያብራራ ምዕራፍ ነው።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

- (1) (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ልብህን በርግጥም አስፍቶልህ የራዕይ መውረድንም እንድትወድ አደረገህ።
- (ልብህን ለአንተ አላሰፋንልህም?)
- (2) ወንጀልህንም አራገፍንልህ።
- (3) ያ ጀርባህ ለመሰበር እስኪቀርብ ድረስ ያደከመህን (ወንጀልን) አራገፈልህ። (ያንን ጀርባህን ያከበደውን ሸክምህን አወረድንልህምን? )



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

- (4) ዝናህንም ከፍ አደረግንልህ፤
- በአዛን፣ በኢቃማ እና በሌሎች አጋጣሚዎች በስምህ የምትወሳ ሆነ።
- (መወሳትህንም ከፍ አላደረግንልህም?)

- (5) ከጭንቀትና ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾትና ድሎት አለ።
- (6) ከጭንቀትና ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾትና ድሎት አለ።
- በመሆኑም ይህንን ካወቅክ ሕዝቦችህ አንተን ማስቸገራቸው አያስፈራህ፣ ወደ አላህ ከመጣራትም እንዳያግድህ።
- (7) ሥራህን እንዳጠናቀቅክና እንደጨረስክ ጌታህን በመገዛት ላይ ትጋ።
- (8) ፍላጎትህንና ከጃሎትህን ወደ ጌታህ ብቻ አድርግ።

## ከሱረቱ አሽ ሸርህ ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

አላህን ከማምለክ ስትጨርስ ወደ ዱንያ ስራ ቀጥል የሙስሊም ምሁራኖች ይህ አንቀፅ ዛሬ ዐለም እየተቸገረበት ያለዉን የስራ አጥነትን ችግር በአጬሩ የፈታ ነው ይላሉ፡፡ ምክንያቱም የሙስሊም ጊዜ መቼም ቢሆን እረፍት የለዉም፡፡ ከዱንያ ስራ ካረፈ ወደ አኺራ ስራ መጣጣር አለበትና፡፡

- 1. አላህ ነብዩን ሰ.ዐ.ወ ልባቸውን በመክፈት ወንጀላቸውን በመማርና ክብራቸውን ከፍ በማድረግ፤ የሙዕሚን ልብ ለዲን መከፈቱና ችግሮችን ለመሸከም መታደሉ ትልቅ ፀጋ መሆኑ፤
- 2. ሁልጊዜም ከችግር በስተኋላ የነገሮችን መቃለል እንዳለ ማስተማር፤
- 3. ዱንያ ከጭንቀትና ከችግር ሁልጊዜም ነፃ እንደማትሆን፤



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ አካዳሚ

## ከሱረቱ አሽ ሸርህ ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

- 4. የሰው ልጅም በችግር ጊዜ ትዕግስት እንዲኖረውና በደስታ ጊዜም አላህን ሊያመሰግን እንደሚገባው፤
- 5. ቀደም ሲልም የነበረበትን ችግርም ሆነ ተድላ ዘወር ብሎ ማስተዋል እንዳለበት፤
- 6. ይህን ሁሉ ፀጋ ስለለገሰው ጌታው አላህ ዘወትር ምስጋና ማድረስ ግዴታው ነው፡፡
- 7. ወንጀል የነቢዩን (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) ጀርባ አክብዶ ከነበረ የተቀሩት ሰዎችስ እንዴት ይሆናሉ።



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com